በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# የመጨረሻ ክፍል

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፳፩ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# የኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ መስፈርቶች

- የኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያኖች ጋብቻ ቅዱስ፣ ሃይማኖታዊና በማይበጠስም ማሰሪያ የታሰረ ግኑኙነት ነው
- ምስጢረ ተክሊሉም ኦርቶዶክሳዊ በሆነ ወንድና ኦርቶክሳዊ በሆነች ሴት መካከል በግልጥ ይፈጸማል፡፡
- ይህን በመሰለ መንገድ የጋብቻን ሕይወት የሚጀምሩ መልካም ቤተሰብ መመስረትም ይቻላቸዋል፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ የክህነት ሥልጣን በተሰጠው ካህን ወይም በሰጠው ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ አማካይነት የሚፈጸም ምስጢር ነው፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ ያለተጋቢዎቹ ፈቃድ ሊፈጸም አይችልም፡፡
- ተጋቢዎቹም ወንዱ ከሃያ ዓመት ያላነሰ ሴትዋም ከአስራ አምስት ዓመት ያላነሰ ዕድሜ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ የሥጋ ወይም የመንፈስ (ክርስትና አባት ወይም እናት) ዝምድና ባላቸው፣ ወይም በአሳዳጊና በማደጎ ልጅ መካከል እንዲፈጸም አይፈቀድም፡፡ *ማር 6፡17፣ ማቴ 14፡1-12፡፡*
- በክርስትና ከአንድ በላይ ማግባት ስለማይፈቀድ ከአንድ በላይ ማግባት ዝሙት ነው፡፡
- በማመንዘር የፈታ ሰውን ማግባትም ዝሙት ነው፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ያልሆነ ሰውን ማግባት አይፈቀድም፡፡ *ዘሌዋ 18፡6፣ 21፡20፣ ዘዳግ 7፡3-4፡፡*
- የሰውነታቸውን ፈቃድ ለመፈጸም የማያስችል ሕመም ባላቸውና የአእምሮ መታወክ ባላቸው መካከልም ጋብቻ አይፈጸምም፡፡
- ከተጋቡ በኋላ በሕክም ሊታከም የማይችል መካንነት ቢገጥምም ፊች ኤአፈቀድም፡፡

# የኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ መስፈርቶች

## *የጋብቻ ሥነሥርዓት የሚፈጸምባቸው ቅደም ተከተሎች*

- ከሁሉ አስቀድሞ ተጋቢዎቹ የንስሐ አባት ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸውን፣ ትውፊታቸውንና ቀኖናቸውን እንዲሁም ስለ ጋብቻ ሕይወት በአግባል መማርና ማወቅ፡፡
- ተጋቢዎቹ (ወንድና ሴት) አስቀድሞ ጋብቻ ያልፈጸሙ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ከሚኖሩበት ቀበሌ ማቅረብ፡፡
- ከላይ የተጠቀሱትን ካሟሉ ከንስሐ አባታቸው ጋር በመሆን፣ የቀበሌ ደብዳቤያቸውን ከሁለት ጉርድ ፎቶግራፎች ጋር በመያዝ የጋብቻቸው ሥርዓት ወደሚፈጸምበት ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ማመልከቻቸውን ማቅረብ፡፡
- የፊርማ ሥነሥርዓት እንዲፈጸምላቸው በተቀጠሩበት ዕለት በወንድም ሆነ በሴት በኩል የተጠየቁትን ሽማግሌዎች በመያዝ ከንስሐ አባታቸውነ ጋር ሆነው በቤተ ክርስቲያኒቱ የጋብቻ ባሕረ መዝገብ ላይ ፊርማቸውን ማኖር፡፡
- ሥርዓተ (ምስጢረ ጋብቻ) ሊፈጸምላቸው በተቀጠሩበት ዕለት በተገለጸላቸው ሰዓት ቀለበታቸውን በመያዝ ቀደም ብሎ በመገኘት ከጸሎቱ ጥልቅ ተሳትፎ በማድረግ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል፡፡
- በማስከተልም የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጋዊ ማኅተም ያረፈበትን የኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ ማረጋገጫ በካህናቱና በምዕመናኑ ፊት ከተነበበላቸው በኋላ መቀበል፡፡

# የኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ መስፈርቶች

## *ጋብቻ ተቀባይነት የማያገኝባቸው ምክንያቶች*

- ተጋቢዎቹ ለመጋባት ያልወሰኑ ሆነው ቢገኙ
- ጋብቻቸው በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በምስክሮች ፊት ያልተፈጸመ ሆኖ ቢገኝ
- ተጋቢዎቹ ለጋብቻ በሚያበቃ የዕድሜ ክልል ያልተገኙ ቢሆኑ
- ተጋቢዎቹ ለጋብቻ የሚሆን እንቅፋት ምክንያት ቢገኝባቸው
- ከሁለት አንዳቸው ጋብቻ የፈጸሙ መሆኑ ቢረጋገጥ
- በዝሙት የተነሳ ፊቺ የፈጸሙ መሆናቸው ቢረጋገጥ
- በጠለፋ (በኃይል) ጋብቻው ሊፈጸም እንደሆነ ቢረጋገጥ

## *የፍቺ ምክንያቶች*

- ከሁለት አንዱ በሞት ከተለዩ
- ከሁለት አንዱ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸውን ትተው መናፍቅ ወይም ከሃዲ ቢሆኑ፣ ከጋብቻ ውጪ ከሌላ ጋር ወድቀው ቢገኙ (ቢያመነዝሩ)፣ ከጋብቻ ውጪ የተጻጻፉት ደብዳቤ ቢገኝ፣ ባል ታሞ ወይም ለረጅም ጊዜ ወደ ሩቅ መንገድ ሄዶ ሳለ ሚስቲቱ ከሌላ ጸንሳ ብትገኝና
- በግብረ ሰዶማዊነት የተነሳ፡፡ ዘዳግ 24፡1፣ ሚል 2፡14-16፣ ቀዳ ቆሮ 6፡12-17፡፡

# የኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ መስፈርቶች

## *ፍቺ ተቀባይነት የማያገኝባቸው ምክንያቶች*

- ተጋቢዎቹ ችግሩ እያለም ቢሆን ተቻችለው ለመኖር ቢስማሙ
- ስለፍቺያቸው ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ከሁለት አንዳቸው በሞት ቢወሰዱ፤ ስለፍቺያቸውም የመጨረሻው ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ማግባትም አይፈቀድላቸውም፡፡

## *ፍቺ ከተፈጸመ በኋላ*

- ሁለቱም ከገቡት ቃልኪዳን ነጻ ይሆናሉ፡፡
- ፍቺው በባል ጥፋት ምክንያት ተደርጎ ከሆነ ሚስት ሌላ ባል እስክታገባ ወይም እስከ ዕለተ ሞትዋ ድረስ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡
- ፍቺ ልጆች ለወላጆቻቸው ያለባቸውን ኃላፊነት በተመለከተ የሚያፋልሰው የለም፤ ልጆች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሁሉ በአግባብ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

*በመጨረሻም ታህሳስ 1 2001 ዓ.ም. እና ጥር 6 ቀን 2001 ዓ.ም. ስለ ጋብቻ የተሰጡ ትምህርቶችን ይመልከቱ ዘንድ አሳስባለሁ፡፡*

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ቅድመ ጋብቻ

## ክፍል 2

## የጋብቻ ዓላማ ምንድር ነው፤ ሥርዓተ ተክሊል ለማን ይፈጸማል፤ ከጋብቻ አስቀድሞ መታወቅ የሚገባቸው ጉዳዮች ምንድር ናቸው?


በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ


ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት


ታህሳስ ፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# ቅዱስ ጋብቻ

የጋብቻ ዓላማ

ሥርዓተ ተክሊል ለማን ይፈጸማል?

የተለያየ መታወቅ የሚገባቸው ጉዳዮች


የጋብቻ ዓላማ
ለመረዳዳት
- ዘፍጥረት 2 * 20 እና መክብብ 4 * 9 — 11
ዘር ለመተካት
- ዘፍጥረት 1 * 25 እና መዝሙር 126 * 3
ከፍትወት ወይም ከዝሙት ለመጠበቅ
- 1ኛ ቆሮ 7 * 8 - 9 ፣ 1ኛ ቆሮ 5 * 1 ፣ ምሳሌ 6 * 30 — 32

# የጋብቻ ሕግጋት

1. ከተጋቡ በኋላ አንድ አካል ናቸው:: ማቴ 19 * 4 — 6
2. መፋታት ክልክል ነው:: ሚል 2 * 14
3. አንድ ወንድ ለአንድ ሴት:: 1ኛ ቆሮ 7 * 2
4. የሚገባቸውን ሁሉ መጠበቅና ማድረግ:: 1ኛ ቆሮ 7 * 3
5. ባልም ሚስትም በራሳቸው ሥልጣን የላቸውም:: 1ኛ ቆሮ 7 * 4
6. ኃላፊነትን መወጣት:: ኤፌ 5 * 20 — 23 ፤ ቆላ 3 * 18 -19::
7. ለጾምና ለጸሎት ካልሆነ አለመለያየት:: 1ኛ ቆሮ 7 * 5
8. ሥጋዊ ጌጥ አለማብዛት:: 1ኛ ጴጥ 3 * 1 - 4
9. ድንገተኛ ግጭት ቢከሰት ወዲያው መታረቅ:: 1ኛ ቆሮ 7 * 10-11
10. በሞት ካልሆነ አለመለያየት:: 1ኛ ቆሮ 7 * 39 እና ሮሜ 7 * 2 -3
11. ከሥጋዊ፤ መንፈሳዊ፤ የጋብቻ ዘመድ አለማግባት::
    ዘሌ 18 * 6-20፤ ዘሌ 20 * 16-21፤ ማር 6 * 17::

## የጋብቻ ሕግጋት የቀጠለ...

1. ልጅ በሥጋ ዝምድና የሚከተሉትን አያገባም፡፡
   - የቅድመ አያቱን እናት፤ እህት፤ ሚስት፤ ልጅ
   - የአያቱን እናት፤ እህት፤ ሚስት፤ ልጅ
   - የአባቱን እናት፤ እህት፤ ሚስት፤ ልጅ
2. አባት በሥጋ ዝምድና የሚከተሉትን አያገባም፡፡
   - የሴት ልጁን፤ የልጅ ልጁን፤የልጅ ልጁን ልጅ
   - የወንድ ልጁን ሚስት፤ የሚስቱንም አያት ፣ እናት ፣ እህት ፣ ልጅ
   - የልጅ ልጁን ሚስት፤ የሚስቱንም አያት ፣ እናት ፣ እህት ፣ ልጅ
   - የልጅ ልጁን ልጅ ሚስት፤ የሚስቱንም አያት ፣ እናት ፣ እህት ፣ ልጅ ፡፡
3. በጋብቻ ዝምድና ባል/ሚስት የሚከተሉትን አያገቡም፡፡
   - የሚስቱን አያት፣ እናት ፣ አክስት ፣ እህት ፣ ልጅዋን ፣ የልጅ ልጇን
4. በመንፈሳዊ ዝምድና
   - የክርስትና ልጅ የክርስትና አባቱን ሚስት፣ እህት፣ ልጁን፣ የልጅ ልጁን
   - የክርስትና አባት የክርስትና ልጁን እናት፣ እህት፣ ሚስት፣ ልጅ፣ የእህቱንና የወንድሙን ልጅ አያገቡም፡፡

- በሃይማኖት አንድ ያልሆኑ አይጋቡም፡፡
- መፋታት ባይፈቀድም ፍቺ በዝሙት (ሥጋዊና መንፈሳዊ) የተነሳ ሊከሰት ይችላል፡፡
- ሌላ ማግባት የሚቻለውም በዝሙት ፍቺና በሞት የተነሳ ብቻ ነው፡፡

# ተክሊል የሚገባው ለማን ነው?

1. ሥጋዊ ድንግልና ላላቸው። ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 906
   - በሕክምና የተነሣ ድንግልናቸውን ያጡ
   - በተፈጥሮ ሲወለዱ የድንግልና ምልክት የሌላቸው
   - ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ ተገደው የተደፈሩ
   - ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ በመሥራት ድንግልናቸውን ያጡም አይከለከሉም።

2. የሃይማኖት አንድነት ላላቸው። 2ኛ ቆሮ 6 * 14 - 18

3. ከ 20 በላይ የሆነ ወንድና ከ15 ዓመት በላይ ለሆነች ሴት።
   ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 883-884 እና አንቀጽ 24 * 894

4. ፈቃደኝነታቸውን ለገለጹ ተጋቢዎች። ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 906

ጸሎተ ተክሊል ከቅዳሴ በፊት የሚፈጸም ሲሆን ያለ ሥጋ ወደሙም አይፈጸምም።

ከላይ የተጠቀሱትን ማሟላት ያልተቻላቸው ተጋቢዎች በሙሉ ጸሎተ ንስሐ ወይም ፍትሐት ዘወልድ ተነቦላቸው ቅዱስ ቁርባን ተቀብለው ኑሮአቸውን ይጀምራሉ።

# መተጫጨት

*በመተጫጨት ሂደት በወንዶች የሚፈጸም ስህተት*

1. የሌለን ሀብት፤ ማዕረግ አለኝ ማለት

2. ደመወዝን ከፍ አድርጎ መናገር

3. ከጋብቻ በፊት ፈቃደ ሥጋን ለመፈጸም መፈለግ

4. አንድ ለአንድ ብቻ መፈቀዱን እያወቁ ብዙ ሴቶችን መከጀል

5. ከእውነተኛ ፍቅር ይልቅ በገንዘብ ለመግዛትና ለመቆጣጠር ማሰብ

6. ራስን ንጹሕ አድርጎ ሌላውን ሰው ማማትና ወዘተ… በዚህም የተነሳ እውነቱ ሲታወቅ አመኔታ ይጠፋል ጭቅጭቅ ይነግሳል።

# መተጫጨት የቀጠለ...

*በመተጫጨት ሂደት በሴቶች የሚፈጸም ስህተት*

1. ፍቅርን ሳይሆን ገንዘብና ሀብትን ብቻ መመልከት

2. ክፉ ባልንጀሮችን በመከተል ለዝሙትና በአለባበስም ምቹ ላልሆነ ሕይወት መጋለጥ

3. የተለያየየ ወንዶችን በእጮኛነት ማቅረብና ዕድሜን መጨረስ

4. ከተዋወቁት ሁሉ ወንድ ጋር መላፋት።

ሴቶች ሆይ፡- መተጫጨት ማለት መጋባት ማለት ስላልሆነ የሁለት ደቂቃ ቀልድ የአንድ ሰዓት ልፊያ አስከትሎ ይኸም ልፊያ የማይጠፋ ጸጸት እንዳያተርፍ መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

# በትዳር ጓደኛ ምርጫ ስኬታማ ለመሆን

1. መንፈሳዊ ሕይወትን አስተካክሎ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ።

2. እውነተኛ መሆን - ለማግኘት ስንል የሌለንን አለን አለማለት።

3. አንድ ወጥ ጠባይ ያለን መሆን፡- የምንውልበትን ቦታ፤ የምናበጃቸውን ጓደኞች፤ አነጋገራችንንና አካሄዳችንን መወሰን።

4. በዓላማና በአስተሳሰብ አንድነት መቀራረብ

5. የአንድ ሃይማኖት ተከታይ መሆን

6. የንስሐ አባቶችን ምክርና መመሪያ መከተል።

# ቃል ኪዳን

ጽኑእ የፈቃድ ውል። እውነተኛነቱንም ለማረጋገጥ በእግዚአብሔር ስም ቀለበት በማሰር ይፈጸማል።

*ቀለበት፡-*

ክብነቱ፡- ጋብቻው መፋታት የሌለበት መጨረሻ የሌለው መሆኑን ማመልከቻ ሲሆን

የፍቅር ምልክት ነው። #እንደ ቀለበት በልብህ አኑረኝ; መኃ. 8 * 6

በአጠቃላይ የቃልኪዳን ምልክት ነው።

*#አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ እርሱንም አምልክ በስሙም ማል።; ዘዳግም 6 * 13።*

*#በስሜም በሐሰት አትማሉ፥ የአምላካችሁንም ስም አታርክሱ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።;*
ዘሌዋውያን 19 * 12

# በአጠቃላይ ከጋብቻ በፊት ምን እናድርግ?

1. በፈሪሐ እግዚአብሔር ለመመላለስ መወሰን

#በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ቅን የሆነውን ነገር ስታደርግ ለአንተ ከአንተም በኋላ ለልጆችህ ለዘላለም መልካም ይሆንላችሁ ዘንድ እኔ የማዝዝህን እነዚህን ቃሎች ሁሉ ሰምተህ ጠብቅ። ; ዘዳግም 12 * 29።

2. በንስሐ ሕይወት ተጠብቆ መኖር።

ራእይ 3 * 19።

3. የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት መጠየቅ።

ትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 1 እና 2።

4. የአካልና የአእምሮ እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ብስለት ያለን መሆናችንን መመዘን። 1ኛ ቆሮ 13 * 11፣ 2ኛ ጴጥ 1 * 5 -10

5. ራሳችንን መቻል። ዘፍ 18 * 14፣ ዘፍ 3 * 17 ፣ 2ኛ ተሰ 3 * 10 – 12

# የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ይታወቃል?

1. ማመንና መወላወል በሌለበት ፍቅር
2. እየጠወለገ ሳይሆን እየለመለመ በሚሄድ ግኑኝነት
3. ፈተና ሲያጋጥም ሳይሸነፉ በትዕግሥት በጋራ በመወጣት

ዮሐንስ 4 ፡ 18

# ልናውቃቸው የሚገቡን

1. በድንግልና ለመኖር ወስኖ ቃልኪዳኑን ትቶ የሚያገባ ቃል ኪዳኑን አፍርሷልና ጸሎተ ተክሊል ሳይፈጽሙለት በቁርባን ብቻ ማጋባት የተፈቀደ መሆኑን፡፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 * 834 ፣ ዘኍ 30 * 2

2. ሚስት ስትጸንስና ከወለደች በኂላ ለተወሰኑ ቀናት ግኑኝነት አለማድረግ፡፡ ፍትሐ ነገሥት አ. 24 * 838፣ ዘሌዋ 20 * 18

3. ጃንደረባ ለሆነ ሰው፣ አእምሮ ለጎደለውም እብድ ሰው ሥርዓተ ተክሊል ፈጽሞ ማጋባት አይገባም፡፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 * 857

4. የሚያገቡ ከሆነ፡- ባል ሚስቱ ስትሞትበት ከአንድ ዓመት በኂላ ሚስትም ባሏ ከሞተ ከ10 ወር በኂላ ከሐዘናቸው ተጽናንተው ያግቡ፡፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 * 916

5. ዘርን ከሴት ማኅፀን አውጥቶ በውጪ ማፍሰስ በደል ነው፡፡ ዘፍጥ 38 * 9-11

ይቀጥላል…

መስብሐት
ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ቅዱስ ጋብቻ

## ክፍል ፮

## ተክሊል እና የጥያቄዎቻችሁ መልሶች

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

## በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
ጥር ፮ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# ምስጢረ ተክሊል

- ተክሊል ማለት:- «ተከለለ» ተቀዳጀ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የወጣ ነው በጋብቻቸው ጊዜ ሙሽራው እንደ ንጉሥ፣ሙሽራዩቱ እንደ ንግሥት ኹነው አክሊል ይቀዳጃሉና::

- ጋብቻ እንደ አዳምና ሔዋን አንድ ወንድ ላንድ ሴት፣ አንድ ሴት ላንድ ወንድ ነው::

- አሕዛብ ግን ጋብቻቸው መመሪያ ስለሌለው የብሉይ ኪዳንንም ትምህርት አካተው ስለማያውቁ አንድ ወንድ ብዙ ሴቶችን ያገቡ ነበር::

- ይህም ብዙ የማግባት ልማድ በአሕዛብ ብቻ ሳይሆን በሴማውያንም ዘንድ በአንዳንድ ምክንያት አልፎ አልፎ ይደረግ ነበር:: ነገር ግን ለምስክር ያህል ያንድ ላንድ ጋብቻን ጠብቀውና አክብረው የኖሩ ከአበው እነ ኖህ ነበሩ:: ዘፍጥ 7*7::

# ምስጢረ ተክሊል ...

- በሐዲስ  ኪዳንም በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ያለው ተዋሕዶ በጋብቻ ተመስሏል። እሱ ሙሽራዋ ቤተ ክርስቲያን ሙሽራው ክርስቲያናዊ ጋብቻን ምሥጢር ሊያስገኘው የበቃውም ይኸ ነው። ኤፌ. 5*23-32።

*የጋብቻ ሥነ ሥርዓት፡-*

- በሃይማኖት ከማይመስሏቸው ጋር እሥራኤል አይጋቡም ነበር። ዘሌዋ. 18*6። 21*20። 1-21። ዘዳግ. 7*3-4።
- በሐዲስ ኪዳንም ዝምድናቸው ካልተራራቀ ዘመዳሞች አይጋቡም። ዋርሳ መውረስም ተክልክሏል። እንዲያውም እነ ዮሐንስ መጥምቅ አንገታቸውን የሰጡት የዋርሳን ሥርዓት በመቃወም ነው። ማር 6 * 17። ማቴ 14*1-12።
- በሃይማኖትና በዶግማ የማይመሳሰሉም አይጋቡም። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ግን ወንዱ ክርስቲያን ኹኖ ሴቷ ክርስቲያን ባትኾን ወይም እሷ ክርስቲያን ኹና ወንዱ ክርስቲያን ባይኾን እነዚህ ለመጋባት ቢፈልጉ እሱ እሷን አስጠምቆ ወይም እሷ እሱን አስጠምቃ ሊጋቡ ይችላሉ። ያለዚያ ግን ክልክል ነው። ጋብቻው ከክርስቶስ ፍቅር ሊለይ አይችልምና፤ በክርስቶስ ያልተባረከ ጋብቻ ከዝሙት ይቆጠራል። 1ኛ ቆሮ 6*12-17።
- የማግባት ያህል ካገቡም በኋላ መፍታቱ ለአሕዛብ ልማድ ቀላል ሲኾን በብሉይ ኪዳን ግን ይልቁንም በሥነ ፍጥረት ያልነበረ ነው። መድኃኒታችን ለፈሪሳውያን እንደ መለሰላቸው ሙሴ የመፍታትን ሕግ የሠራው ዘዳግም. 24*1። በእሥራኤል ክፋት እንጅ ከጥንት ከሥነ ፍጥረት አይደለም። ነቢያትም የመፋታትን ሕግ ያወግዙ ነበር። ሚልክ. 2*14-16።

# ምስጢረ ተክሊል …

-በአዲስ ኪዳንም ጌታችን እንዳስተማረው በዝሙት መክንያት ካልኾነ በቀር ከሳች ጠቆረች፣ መከነች፣ ደረቀች ብሎ ሚስቱን መፍታት አመንዝራነት ነው::ማቴ 5* 32:: ሉቃ 16*18:: ቀዳ ቆሮ 7*10:: ከኹለት አንዱ በሞት ከተለየ ግን በሕይወት የቀረው ለማግባት ይፈቀድለታል።

- በትምህርተ አበው መሠረት ተክሊል ከቅዳሴና ከቁርባን ጋር የተያያዘ ነው:: ሙሽሮች ቆመው አስቀድሰው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ፤ ከዚያም በሚዜዎቻቸውና በዕድምተኞች ታጅበው ወደ ሙሽራው ቤት ይጓዛሉ:: ከዚያ በኋላ የሚፈጸመው ኹሉ እንደየሀገሩ ባህልና ልማድ ነው::
- አምብሮስዮስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን አባት በሀገረ ስብከቱ በሚላኖ ስለ ክርስቲያኖች ጋብቻ ሲገልጥ እንዲህ ይል ነበር:: «ከቤተ ክርስቲያን ተመልሰው ወደ ሙሽራው ቤት ይሄዳሉ፣ ከበሩ ሲደርሱ ሙሽራይቱ ጠጉሯን ወይም የጠጉሯን ማሠሪያ ሻሿን፣ ዓይነ ርግቧን ትፈታለች የባሏ እንጅ የሌላ አለመሆንዋን ለመግለጥ ነው:: እሱም የቤቱን ቁልፍ ያስረክባታል:: የቤቱ ባለቤት እሷ መኾንዋን ለመግለጥ ነው::»
- በምሥራቅ ሶርያ የሚኖሩ  ክርስቲያኖች ደግሞ ሥርዓተ ተክሊሉን በቤተ ክርስቲያን ከፈጸሙ በኋላ ወደ ቤታቸው ተመልሰው የሚፈጽመት ተጨማሪ ሥርዓት አላቸው:: በጽዋ ወይንና ውሃ ቀላቅለው ይጸልዩበታል:: ከጸሎቱ በኋላ ከመቃብር ሰማዕታት አፈር ዘግነው አምጥተው ከጋብቻው ቀለበት ጋር ወደ ጽዋው ይጨምሩታል ሙሽራውና ሙሽራይቱ ከዚህ ጽዋ  ፉት ፉት ብለው ቀምሰው ቀለበቱንም በጣታቸው ያገቡታል፤ በራሳቸው ላይ የሚደረገው ተክሊል ደግሞ፤ ቀይ ነጭና ሰማያዊ ፈትል አንድ ላይ ገምደው ነው፣ ዛሬም በአርመን ቤተ ክርስቲያን ለተክሊል የሚጠቀሙበት ይህንን የሐር ገመድ ነው::

# ምስጢረ ተክሊል ...

- ጋብቻን የሚከለክሉ ገደቦች ጠብቀው ከአሥራ አምስት ዓመት ያላነሰ ዕድሜ ያላት ድንግል ቆንጆ ከሃያ ዓመት ያላነሰ ዕድሜ ያለው ድንግል ጎበዝ፣ በወላጆቻቸው አማጭነት፣ ያለዚያም በቤተሰብ ተጠያይቀው ጋብቻን ለመፈጸም ይችላሉ ከጋብቻው ቀደም ሲል ግን ኹለቱ እጮኞች በወላጆቻቸውና በመምህረ ንስሐቸው የውዴታ ቃላቸውን ከሰጡና ፈቃደኛነታቸው ከገለጡ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን የተክሊል ክፍል ሔደው የጋብቻ ደንብ የሚያዘውን ያሟላሉ:: ከዚህ በኋላ የተክሊል ሥርዓት ይፈጸማል::
- ከተክሊሉ ቀደም ሲል የሚፈጸመው የቀለበት ቃል ኪዳን ነው:: በኹሉም የነፍስ አባት ቄስ አይለይም:: ሥራውን የሚመራው እሱ ነውና:: የክርስቲያኖች ጋብቻ: ብዙውን ጊዜ የሚፈጸመው እሑድ ነው:: በሰባቱ አጽዋማት ጋብቻ አይፈጸምም::

*<u>በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የተክሊል አፈጻጸም ሥርዓት:-</u>*

- ቅዳሜ ለእሑድ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ሙሽራው ከሚዜዎቹና ከቤተ ዘመዱ ጋር፤ መሽራይቱም ከዘመዶቿና ከሚዜዎቿ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው የተመደበላቸውን ቦታ ይይዛሉ::
- ሙሽራው ከነተከታዮቹ በሰሜናዊ ማዕዘን፣ መሽራይቱ ከነተከታዮቿ በደቡባዊ ማዕዘን ይቆማሉ:: ተክሊሉ የሚፈጸምበት ሰዓት ሲደርስ በምዕራቡ በኩል ከመካከለኛው ክፍል በድርገት መውረጃው በቅድስቱ የተክሊል መፈጸሚያው ክፍል ይዘጋጃል:: ኹለቱም ሙሽሮች ባንድ አግዳሚ መቀመጫ ያለዚያም በኹለት ወንበሮች ግራና ቀኝ ይቀመጣሉ::
- መሽራይቱ የምትቀመጥ በቀኝ ነው:: በፊት ለፊታቸውም የሚቀዳጁት አክሊል የሚቀቡት ዘይት፣ የሚለብሱት ልብሰ ክህነት፣ እነዚህ ኹሉ በሙሽሮቹ ፊት በጠረጴዛ ይቀመጣሉ::
- ከዚህ በኋላ የተክሊሉ ጸሎት ይጀመራል በልብሶቹ ላይ የሚጸለየው ጸሎት ሲፈጸም ቄሱ ባርኮ ያለብሳቸዋል:: የዘይት ጸሎት ሲፈጸም ግንባራቸውን በትእምርተ መስቀል ይቀባቸዋል:: የአክሊሉ ሲፈጸም ባርኮ በየራሳቸው ላይ ያደርግላቸዋል:: ከዚህ በኋላ ማጠቃለያ የቡራኬ ጸሎት አድርሶ ሲፈጽም ጸሎተ ቅዳሴው ይጀመራል:: አስቀድሰው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ ቃል ኪዳናቸውን በሥጋውና በደሙ ያጸናሉ::

# ምስጢረ ተክሊል ...

- ያለ ቁርባን የሆነ ተክሊል፡ ተክሊል አይባልም፡፡በዝሙት በሃይማኖት በሞት ምክንያት ካልኾነ በቀር ባልና ሚስት እንዳይለያዩ ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያት ባንዱ ቢለያዩ ግን ወንድም ኾነ ሴት እንደገና ማግባት ይፈቀዳል ይህ እስከ ሦስት ጊዜ ይኾናል ከዚያ በላይ ግን እንደ ዝሙት ይቆጠራል፡፡
- የተክሊል አፈጻጸም በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ አፈጻጸም አለው፡፡

*በምሥራቅ መለካውያን ዘንድ የተክሊል ሥርዓት በጣም ጥብቅ ነው፡፡*

- የተክሊልን ፈቃድ የሚሰጥ ጳጳሱ ነው፣ ጳጳሱም ካልተገኘ የሰበካው ካህን ለጳጳሱ ጽ/ቤት አሳውቆ ያስፈቅዳል ማዘጋጃ ቤት የጋብቻውን ውል የሚያጸድቀው የቤተ ክርስቲያንን ማኅተምና ፈቃድ የሰጠውን ኤጲስ ቆጶስ ፊርማ ካረጋገጠ በኋላ ነው፡፡
- ጋብቻ በነሱ ዘንድ ሃይማኖታዊ ምሥጢርን የያዘ ቢኾንም በማሕበራዊ ኑሯቸው ደግሞ የቤተሰብ መመሥረቻ ውል ስለኾነ በወንዱና በሴቷ ፈቃድ ብቻ የሚፈጸም ሳይኾን በሕገ መንግሥታቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚደረግለት ተቀደሚ ሕግ ነው፡፡ ያለ ጥሩ ጋብቻ ጥሩ ዜጋ ማፍራት አይቻልምና ይህን የመሰለ አብሮ መሥራት ለቤተ ክርስቲያንም ለመንግሥትም ጠቃሚ ነው፡፡
- ከተጋቡ በኋላ መፋታት ክልክል ቢኾንም በኹለቱ ማለት በባልና ሚስት ስምምነት ሊፋቱ ይችላሉ፡፡ ይህንንም የሚፈቅድ ኤጲስ ቆጶሱ ብቻ ነው፡፡ ማግባት ግን ቢበዛ ከኹለት ጊዜ አይበልጥም፡፡

*በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን*

- በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጥብቅ የጋብቻ ሕግ አላቸው መፋታት ፈጽሞ ክልክል ነው፡፡ ነገር ግን ሕጋቸው መፋታትን ቢያግድም የሃይማኖትን ሥርዓት እምነት እንጅ ዓለማዊው ሕግ ስለማያግዳቸው ከጋብቻ ውጭ ብዙ ስሕተቶች የሚፈጸሙ መኾናቸው ግልጽ ነው፡፡

# ምስጢረ ተክሊል ...

*በፕሮቴስታንት*

- በፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተክሊል ምሥጢርነት የለውም፡፡ ባልና ሚስት ካልተስማሙ በማናቸውም ጊዜ መፋታት ይፈቀዳል፡፡

*ማጠቃለያ*

- ቤተ ክርስቲያናችን በዘመናት ኹሉ ለምዕመኖቿ የምታስተምረው ከላይ እንደገለጥነው ነው፡፡
- ኃጢአትን በየጊዜው መናዘዝና (ንስሐ) የተክሊል ጋብቻ ተረስተው አልፎ አልፎ ካልኾነ በብዛት ሲፈጸሙ አይታዩም፡፡ በርግጥ ዲያቆናት ሲያገቡ በተክሊል ነው ከምዕመናንም አንዳንድ አይታጡም፡፡
- ምሥጢረ ቁርባንንም በመፍራት ብዙዎች ሲሸሹት ይታያሉ፡፡ በርግጥ ሲጠመቁ ጀምረው አካለ መጠን እስኪያደርሱ ይቆርባሉ፡፡
- ከዚያ በኋላ ግን ብዙዎቹ እስኪያረጁ ድረስ አይቆርቡም፤ ለዚህም የሚሰጡት ምክንያት በሕይወታቸው ውስጥ ስሕተት ሊፈጸም ይችላል ነው፤ ታዲያ ግን ኃጢአታቸውን በንሥሐ እየታጠቡ ቢቀበሉት ከተጨማሪ ስሕተት ይጠብቃቸው ነበር፡፡ አንዳንዶቹ በንስሐ እየተመለሱ ይቆርባሉ፡፡ ተገቢውም አኗኗር በንስሐ ተመልሶ በቁርባን ተወስኖ መኖር ነው፡፡

# ተክሊል የሚገባው ለማን ነው?

1. ሥጋዊ ድንግልና ላላቸው፡፡ <u>ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 906</u>
   - በሕክምና የተነሣ ድንግልናቸውን ያጡ
   - በተፈጥሮ ሲወለዱ የድንግልና ምልክት የሌላቸው
   - ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ ተገደው የተደፈሩ
   - ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ በመሥራት ድንግልናቸውን ያጡም አይከለከሉም፡፡
2. የሃይማኖት አንድነት ላላቸው፡፡ <u>2ኛ ቆሮ 6 * 14 - 18</u>
3. ከ 20 በላይ የሆነ ወንድና ከ15 ዓመት በላይ ለሆነች ሴት፡፡
   <u>ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 883-884 እና አንቀጽ 24 * 894</u>
4. ፈቃደኝነታቸውን ለገለጹ ተጋቢዎች፡፡ <u>ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 906</u>

*<u>ማስታወሻ፡-</u>*

1. ጸሎተ ተክሊል ከቅዳሴ በፊት የሚፈጸም ሲሆን ያለ ሥጋ ወደሙም አይፈጸምም፡፡

2. ለተክሊል የሚገባውን ማሟላት ያልተቻላቸው ተጋቢዎች በሙሉ ጸሎተ ንስሐ ወይም ፍትሐት ዘወልድ ተነቦላቸው ቅዱስ ቁርባን ተቀብለው ጋብቻቸው ተባርኮ ኑሮአቸውን ይጀምራሉ፡፡

# በተክሊል ዕለት ማድረግ የሚገባ

1. ሙሽራውና ሙሽሪት ምስጢረ ተክሊል የሚፈጸመው ቅዳሜና እሁድ ከሆነ ከሌሊቱ 10 ሰዓት በሌሎቹ ዕለታት ከሆነ ግን ከሌሊቱ በ11 ሰዓት በቤተክርስቲያን መገኘት
2. በዕለቱ የቃል ኪዳን ቀለበት እንዳይረሳ አስታውሶ መያዝ
3. የሙሽሪት ሚዜዎች አለባበስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የጠበቀ እንዲሆን
4. የፎቶግራፍም ሆነ የቪዲዮ ባለ ሞያዎች ከላይ ነጠላ አደግድገው በመልበስ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ

# ጥያቄዎቻችሁና መልሶቻቸው

1. ዛሬ ከሚገኙ ወላጆች ጋብቻን በተመለከተ ምን እንማራለን?

   *በጋብቻ ሕይወታቸው በጎ ምሳሌነት ካላቸው በጎውን መማርና ራስን በበጎነት መቅረጽ…*

2. ለጋብቻ በዕድሜ መበላለጥ የግድ አስፈላጊ ነው ወይ?

   *ከቤ/ክ በተሰጠን ትምህርት መሠረት ዕድሜ ለብስለት ከሚያስፈልገን በቂ ጊዜ አንጻር ስለሚታይ መበላለጡን መጠበቅ ጠቃሚነት አለው…*

3. በእጮኝነት መቆየት የሚገባው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

   መጀመሪያውኑ ሊጋቡ ወስነው ለተቀራረቡ እጮኛሞች ከሁለት ዓመት ያለአግባብ ያልረዘመ።

4. የሕይወት ጓደኛ ብፈልግም ላገኝ አልቻልኩምና ምን ላድርግ?

   በሌለበት ቦታ ወይም ያለአዘጋጁና ሰጪ ፈልገን ከሆነ የሚገኙበትን መለየትና እግዚአብሔርም ከራሳችን አካል ጋር እንዲያገናኘን መለመን ይጠብቅብናል።

# ቀጣይ ርዕሶች

1. ምትሐት
2. የቤተሰብ ምጣኔ
3. ሙዚቃ
4. እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን በየት ትገኛለች?

# ወስብሐት

# ለእግዚአብሔር።